# ሞት እንግዳ!

(ለሎሬት ጸጋዬ፣ ከነቅዓ ጥበብ፣ ሎንዶን የካቲት 19፣ 1998)



አንተ ሞት እንግዳ፣ ትሆናለህ እንጅ፣
እናውቅህ የለም ወይ! ከከበደ ደጅ፣
ከመንግሥቱ ደጅ።
ከበደ ሚካኤል፣ ያ መንግሥቱ ለማ፣
በሰማዕታቱ፣ በሙታን ከተማ፣
ዛሬም በጸጋዬ፣ መርዷችሁ ተሰማ።

ጸጋዬ ሎሬቱ፣ የቅኔው ሜዐበል፣
በድንገት ጸጥ አለ፣ እንደምን ይባላል?
በሰውኛ ልማድ፣ ህይወቱ አልፏል ቢባል፣
መንፈሱ አላለፈም፣ በውስጣችን ሰርጿል።
ገጸባህርዩ ጎልቶ ይታየናል፣
የቅኔውም ፍሰት ድምጹ ይሰማናል።

እኔ በበኩሌ ማመን ተስኖኛል፣
ቅድምም አሁንም፣ ድቅን ይልብኛል።
የጸጋዬ ድርሰት፣ ትዕይንት በሙሉ፣
በገጸባህርይ የፈጠረን ሁሉ፣
ጸጋዬ ሲያርመን ይሰማናል ቃሉ።

ከጥቁር ተምሮ፣ ነጭን ያስተማረ፣
ከነጭ ተምሮ፣ ነጭን ያስከበረ፣
ራሱን በራሱ፣ የተመራመረ፣
የሰውን ጥንተ-ዘር እትብት የቀመረ፣
በአፍሪቃ ሌጀንድ ማተቡን ያሰረ፣
ለባዕድ አምልኮ፣ ያልተኳረጸረ፣
ለውስጥ ታሪክ በራዥ ክብሩን ያልገበረ፣
በስድስት ወር ሀሁ ትግልን ያስተማረ፣
ለሀገሩ አንድነት፣ እንዳንጎራጎረ፣
ለእማማ ኢትዮጵያ፣ እንዲያ እንደዘመረ፣
የጸጋዬ አንደበት፣ እውን ተሳሰረ?

ያ የትያትር ሊቅ፣ ባህርይ ፈጣሪ፣
ያ ስል ባለቅኔ፣ በምጸት መታሪ፣
ያ የመድረክ ደወል፣ የተኛውን ቀስቃሽ፣
ያ የተውኔት ሞተር፣ በድንን አንቀሳቃሽ፤
ዒላማ የማይስት፣ አነጣጥሮ ተኳሽ፣
የጦቢያ ምርጥ ልጅ፣ ጸጋዬ ሎሬቱ፣
በጠቅላላው ዓለም፣ የተባለው አንቱ፣
እውን እንደዋዛ፣ አለፈ ህይወቱ?
«ከንቱ፣ ኩሉ ከንቱ!
እስመ ኩሉ፣ ኀላፊ ውእቱ።»

ቢፈጥር ቢፈጥር፣ ፍጹም የማይደክመው፣
የጸጋዬ አእምሮ፣ በማን ሊወረስ ነው?
ዘወትር ስለቱ፣ የማይዶለዱመው፣
የጸጋዬን ብዕር የሚወርስ ማን ነው?
ወኔና ኩራቱ፣ የማይፈተነው፣
ኢትዮጵያዊ ልቡ፣ በማን ሊተካ ነው?

የጸጋዬ ብዕር፣ የትም ያፈራቸው፣
የሙያ ልጆቹ፣ አያሌዎች ናቸው።
የአብራኩም ሆኑ፣ የሙያ ልጆቹ፣
ትውፊቱን ያክብሩ፣ ፍጹም ሳይሰለቹ።

ቅርሳችን ነውና ጸጋዬ ሎሬቱ፣
በኢትዮጵያ  መሬት፣ ይተከል ሐውልቱ።
ቅርሳችን ነውና ጸጋዬ ሎሬቱ፣
ከትውልድ ትውልድ፣ ይተከል ሐውልቱ።
ቅርሳችን ነውና ጸጋዬ ሎሬቱ፣
በእያንዳንዳችን ልብ፣ ይተከል ሐውልቱ።